# ስለቅዳሴ



አዘጋጅ፡- መምህር በትረማርያም አበባው

# ስለ ቅዳሴ ክፍል ፩

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ።

አሜን ለታሪክ ሲሆን እውነት፣
አሜን ለሃይማኖት ሲሆን አዎ፣
አሜን ለምረቃ ሲሆን ይደረግልኝ ማለት ነው።

ቅዳሴ ማለት ልዩ ምሥጋና ማለት ነው።የሰው ልጅ የተፈጠረው ፈጣሪን እያመሰገነ በደስታ ይኖር ዘንድ ነው። በቅዳሴ ጊዜ ተሠጥዎ ለመመለስ ብቻ ካልሆነ በቀር ድምጽ ማሰማት አይገባም። አዳም ከተፈጠረ በኋላ በገነት መካነ ጸሎት ለይቶ ይጸልይ ያመሰግን ነበር። ጸሎት ማለትም ምሥጋና ያለበት ልመና ማለት ነው።በሰይጣን ተንኮል አዳም ከገነት በተባረረ ጊዜ እንዲሁ በደብር ቅዱስ የጸሎት ቦታ ለይቶ መሥዋእት ያቀርብና ይጸልይ ነበር። አዳም ከሞተ በኋላ አጽሙን እንደታቦት አድርገው በዚያ መሥዋእት ሲሰው ጸሎት ሲጸልዩ ይኖሩ ነበር።ይህ ሲያያዝ ከኖኅ ደረሰ። ኖኅም ዓለም በማየ አይኅ ስትጠፋ የአዳምን አጽም ወደ መርከብ ይዞት ገብቷል።ከመርከቡ ሲወጣም የአዳምን አጽም እንደ ታቦት አድርጎ መሥዋእት ሰዋ።ከዚያ የኖኅ ልጅ ሴም አጽመ አዳምን ለካህኑ ለመልከጼዴቅ አስጠብቆታል።

ከዚህ በኋላ የተነሱት አበው እነ አብርሃም እነ ይስሐቅ እነ ያዕቆብ ሁሉ ቦታ ሳይለዩ በፈለጉት ቦታ መሥዋእት ያሳርጉና ይጸልዩ ነበር። ይህ እስከ ሙሴ ድረስ ዘልቋል። በሙሴ ጊዜ እግዚአብሔር የደብተራ ኦሪትን አሠራር እና የመሥዋእት አቀራረብ እንዲሁም የሚያቀርቡት ካህናት ሌዋውያን አሿሿም

ለሙሴ ገለጠለት። ስለዚህም መሥዋእትም በተለየች ደብተራ ኦሪት (ድንኳን) መደረግ ተጀመረ።ከዚያ በፊት ማንኛውም ሰው መሥዋእት ያሳርግ ነበር።በኦሪት ግን መሥዋእት የሚያቀርቡ ካህናት በተለየ ተመረጡ።በንጉሥ ሰሎሞን ጊዜ ደግሞ ታላቁ ቤተመቅደስ ተሠራ በዚህን ጊዜም ከደብተራ ኦሪቱ የተለየ አልነበረም።ይህ ሲያያዝ እስከ ክርስቶስ ድረስ ቀጥሏል።

ከዚያ በኋላ ሐዋርያት በየደረሱበት ቦታ እየቀደሱ ያቆርቡ ነበር። ከዚያ በፊልጵስዩስ የመጀመሪያዋ ቤተክርስቲያን ተሠራች። ጌታም ሐዋርያትን አቆረባቸው።እርሱም ወይእዜኒ አንትሙኒ ከመዝ ግበሩ ከዛሬ ጀምሮ እናንተም እንደዚህ አድርጉ ብሏቸዋል።ከዚያ በኋላ እነርሱም በቤተክርስቲያን እየቀደሱ ማቁረብ ጀመሩ።ያ ሥርዓት እስካሁን ጸንቶ አሁንም መሥዋእት የሚሰዋባት ቅዳሴ የሚቀደስባት ቤተክርስቲያን ናት። በብሉይ ኪዳን መሥዋእት ሰውተው ከሥጋዊ መከራ ከእለት ችግር ይድኑ ነበር።በሐዲስ ኪዳን ላለን ለእኛ ደግሞ በቅዳሴ መሥዋእት ሲሰዋ ለፍጥረታት ሁሉ ጸሎትን አቅርበን እኛም ከነፍሳዊም ከሥጋዊም መከራ የምናመልጥበት ታላቅ ነገር ነው። ሥለ ወንዞች፣ ስለ ዝናማት፣ ስለ ዓለም፣ ስለ አዕዋፋት፣ ስለ እንስሳት ሁሉ የሚያስፈልጋቸውን ይሰጣቸው ዘንድ ጸሎት የሚቀርብበት ነው ቅዳሴ። ከምንም በላይ ሥጋየን ብሉ ደሜን ጠጡ ባለን መሰረት ደሙ ሥጋው የሚፈተትበት ለእኛም ጸጋን የሚያድልበት ስለሆነ ቅዳሴ በቻልንባቸው ጊዜያት እና አጋጣሚዎች ሁሉ ልናስቀድስ ይገባል። አጠቃላይ ሥለ ሥርዓተ ቅዳሴ እና ሌሎች በቅዳሴ ጊዜ ልናደርጋቸው ስለሚገቡ ነገሮች በቀጣይ ክፍል በሰፊው እንጽፋለን።

## ሰላም ለኩልክሙ

14ቱ ቅዳሴያት የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው።

1 ቅዳሴ እግዚእ

2 ቅዳሴ ማርያም

3 ቅዳሴ ፫ቱ ምእት

4 ቅዳሴ ዮሐንስ ወ/ነጎድጓድ

5 ቅዳሴ ሐዋርያት

6 ቅዳሴ ዲዮስቆሮስ

7 ቅዳሴ ባስልዮስ

8 ቅዳሴ ዮሐንስ አፈወርቅ

9 ቅዳሴ አትናቴዎስ

10 ቅዳሴ ቄርሎስ

11 ቅዳሴ ጎርጎርዮስ

12 ቅዳሴ ጎርጎርዮስ ካልዕ

13 ቅዳሴ ያዕቆብ ዘሥሩግ

14 ቅዳሴ ኤጲፋንዮስ

በእነዚህ ቅዳሴያት ውስጥ አምስቱ አዕማደ ምሥጢር እና ሌሎች የሥነ ምግባር ትምህርቶች በሰፊው ያሉበት ስለሆነ የሚቀደሰው ቅዳሴ ምን እንደሆነ ለማወቅ እና የሚነበበው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ምን እንደሚሆን አስቀድመን ማየት እንድንችል የሚረዳን መጽሐፍ "መጽሐፈ ግጻዌ" ይባላል።እነዚህን 14ቱን ቅዳሴያት የያዘው መጽሐፍ ደግሞ "መጽሐፈ ቅዳሴ" ይባላል። ገዝተን ልናነበው እንችላለን።መደቡ ከመጽሐፈ ሊቃውንት ውስጥ ነው።

ቅዳሴ ስናስቀድስ ዜማው የሚባለው ወይም የሚዜመው በግእዝ ቋንቋ ስለሆነ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ክርስቲያን ግእዝ ቋንቋን ጠንቅቆ ማወቅ አለበት።አለበለዚያ የሚባለውን ሳያውቅ ዝም ብሎ መቆም ብቻ ይሆንና

ተመስጦ ሳይኖረው በድካም በመሰልቸት ይጨርሳልና ነው።በቅዳሴ ጊዜ ዲያቆኑ በየመካከሉ የሚለው "ተንስኡ ለጸሎት" ለጸሎት ተነሱ ማለት ሲሆን ምስጢሩ አዳምን ጌታ ከ5500 ዘመን በኋላ አድንሀለሁ ብሎት ስለነበር ያንን  በተስፋ ይጠብቅ ስለነበር ቀኑ ሲደርስ በእለተ ስቅለት አርብ ቀን አዳም ልጆቹን ተንስኡ ለጸሎት አላቸው። እነርሱም "እግዚኦ ተሣሀለነ" አቤቱ ይቅር በለን።ብለው እግዚአብሔርን ይማጸናሉ።በመካከል ጌታ በአካለ ነፍስ ወርዶ "ሰላም ለኩልክሙ" ሰላም ለሁላችሁ ይሁን አላቸው።

## 41 ጊዜ እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ

በቅዳሴ ጊዜ እግዚኦታ 41 ጊዜ ነው። ይህ 41 የሆነበትም የራሱ ምሳሌ አለው።አዳም እጸ በለስን በልቶ ከገነት በተባረረ ጊዜ እግዚአብሔር መሐሪ ስለሆነ እንዲምረኝ ብሎ ሱባኤ ገባ። ነገር ግን ሰይጣን ገብርኤልን ሳይሆን ገብርኤል ነኝ ብሎ ሱባኤ ይዘው ሳለ በ35ኛው ቀን ሱባኤውን ለማፍረስ መጣ። እግዚአብሔር ምሯችኋል ውጡ ብሎ የውሸት ስብከት ሰበካቸው።እነርሱም የእርሱን ቃል ሰምተው ከባሕር ወጡ።ከዚያ ብዙ መንገድ ከሄዱ በኋላ አወቃችሁኝ ወይ አላቸው። ገብርኤል ነኝ አላልከንም ወይ አሉት። አይደለሁም እኔ ሰይጣን ነኝ።አስቀድማችሁ የፈጣሪን ትእዛዝ ሻራችሁ ዛሬ ደግሞ ሱባኤ አቋረጣችሁ እንግዲህ እግዚአብሔር አይምራችሁም ብሎ ተስፋ አስቆራጭ ነገር ተናግሮ ድንጋይ አንስቶ ወረወረባቸው። ወተደብተረት ይእቲ እብን ይላል።ያች ድንጋይ ድንኳን ሆናቸው 3 ቀን ተቀመጡ።ከዚያ ከድንኳኗ ወጥቶ ሳለ አዳምን ሰይጣን በሞትና በሕይወት መካከል አድርጎ ደብድቦት ሄዷል።በዚያ አዳም 3 ቀን ተቀምጧል። ከላይ 3 ከዚህ 3 ስድስት ይሆናል።6 እና 35 ሲደመር 41 ይሆናል። ከዚያ አዳም ደሙን ለውሶ መሥዋእት አቀረበ። እግዚአብሔርም

አዳም ሆይ በእሩቅ ብእሲ ደም አትድንም ከአሁን በኋላ ደምህን መሥዋእት እንዳታደርግ ብሎ ነግሮ ከልጅ ልጁ ተወልዶ እንደሚያድነው ተስፋ ሰጥቶታል። 41 እግዚአ መሐረነ ክርስቶስ የዚህ ምሳሌ ነው።

ድርገት ሲወርድ መስገድ እጅ መንሳት ይገባል። ይኸውም በትንሳኤ ጊዜ ቅዱሳት አንስት ለክርስቶስ የመስገዳቸው ምሳሌ ነው።ከቁርባኑ በኋላ ዲያቆኑ አንድ ጊዜ ዞሮ ይገባል።ይኸውም ሐዋርያት ይህችን ዓለም ዞረው የማስተማራቸው ምሳሌ ነው።ቅዳሴው እንዳለቀ ካህኑ ሕዝቡን ካህናቱን በእጁ ይባርካቸዋል።ይህም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዕርገት ጊዜ ሐዋርያትን በአንብሮተ እድ የመሾሙ ምሳሌ ነው። ፍትሐት ዘወልድን እና ጸሎተ ንሥሓን ሲጸለይ (ሲደገም) መስገድ ይገባል።

ምስባክ ዲያቆኑ 2 ጊዜ ሕዝቡ 3 ጊዜ ይላሉ።በአጠቃላይ 5 ይሆናል። ይህ አዳም የተፈረደበት የ5500 ዘመን ምሳሌ ነው።በስድስተኛው ካህኑ ወንጌል ይላል።ይህም በስድስተኛው ሺህ እግዚአብሔር አዳምን የማዳኑ ምሳሌ ነው።ወንጌል ማለት የምስራች ማለት ነው።በቅዳሴ ጊዜ መብራት ይብራ።ይልቁንም ወንጌል በሚባልበት ጊዜ አብዝተው ሊያበሩ ይገባል።መብራት መበራቱም ክርስቶስ እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ ያለው ቃል ምሳሌ ነው። በነገራችን ላይ ኪርያላይሶን በግእዝ እግዚአ መሐረነ ክርስቶስ ማለት ሲሆን በአማርኛ አቤቱ ይቅር በለን ማለት ነው።

## *ወደ ምሥራቅ ተመልከቱ*

ዲያቆኑ በቅዳሴ መካከል ከሚላቸው አንዱ ነው።ምሥራቅ የማኅደረ እግዚአብሔር ምሳሌ ነው።አንድም የጌታችንን ነገረ ምጽአቱን አስቡ ሲል ነው።በቅዳሴ ጊዜ ሌላ ዓለማዊ ሀሳብ ልናስብ አይገባም።ከመላእክቱ ጋር

እግዚአብሔርን እያመሰገንን መሆኑን መዘንጋት የለብንም።በሥጋ ከቤተክርስቲያን ውስጥ ሆነን በሀሳብ ግን ሌላ ቦታ ልንሆን አይገባም።ነገራተ እግዚአብሔርን በቅዳሴው ሰዓት የሚነበቡ የወንጌል እና የሐዲሳት እንዲሁም የመልእክተ ጳውሎስ ክፍላትን እንዲሁም አጠቃላይ ካህኑ ዲያቆኑ የሚለውን እኛም የምንመልሰውን ጠንቅቀን ማወቅ አለብን። ለተመስጦ እንዲረዳን ግእዝ ቋንቋውን እንወቀው። እያንዳንዱ የሚደረገው ድርጊት ምሳሌ እና ምሥጢር ስላለው ያንን ጠይቀን ተምረን እንወቀው።

ከቅዳሴ በፊት መሥዋእቱ የሚዘጋጅባት ቤት ቤተልሔም ትባላለች።ቤተልሔም ከዋናው ሕንጻ ቤተክርስቲያን በስተምሥራቅ የምትገኝ ስትሆን ምሳሌነቷ ክርስቶስ ለተወለደባት ቤተልሔም ነው።ከዚያ ከቤተልሔም ወደ መቅደስ ይሄዳል።መቅደስ የቀራንዮ ምሳሌ ነው።የቤተክርስቲያን ውስጠኛዋ ክፍል መቅደስ ትባላለች።በቀራንዮ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ እና ደም እንደፈሰሰ ሁሉ።በዚች መቅደስም የክርስቶስ ሥጋ እና ደም የሚፈተትባት ናትና።ከዚያ ቀጥላ ያለችዋ መካከለኛዋ ክፍል እና ሥጋ ወደሙ የምንቀበልባት ደግሞ ቅድስት ትባላለች።ሊቃውንት ማኅሌት የሚቆሙባት እና መጀመሪያ እንደገባን የምናገኛት ክፍል ደግሞ ቅኔ ማኅሌት ትባላለች።

ከቅዳሴ በፊት ልዑካኑ እንዲሰበሰቡ የሚደወለው የተጋብኦ ደወል ክርስቶስ ይወርዳል ይወለዳል እያሉ ያስተማሩ የቅዱሳን ነቢያት ምሳሌ ነው።ኖኅ በቀን ሦስት ጊዜ ደወል ይደውል ነበር።ይኸውም ጠዋት ለጸሎት ተነሱ ለማለት፣ ከሰዓት ደግሞ የምሳ ሰዓት ደረሰ ለማለትና በሠርክ ደግሞ መሥዋእት ለማሳረግ ነበር። #የግብር ደወል ማለትም ገና ቅዳሴ ሲጀመር የሚደወለው ሲሆን የብሥራተ ገብርኤል ምሳሌ ነው። #የወንጌል ደወል የመጥምቁ ዮሐንስ ስብከት ምሳሌ ነው። #የእግዚአታ ደወል የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት ምሳሌ ነው። #የድርገት ደወል የሐዋርያት

የ፸፪ቱ አርድእት ስብከት ምሳሌ ነው።ምሳሌነቱ እያሰብን ልናስቀድስ ይገባናል።

ጻኡ ንኡሰ ክርስቲያን የሚለው በምጽአት ጊዜ ጌታችን ኃጥዓንን ሑሩ እምኔየ የሚላቸው የመዓቱ ምሳሌ ነው።ወንጌል ከተነበበ በኋላ መጋረጃው (መንጦላእቱ) ይዘጋል። ይኸውም ከምጽአት ፍርድ በኋላ ምንም ዓይነት ምሕረት እንደሌለ የሚያሳይ ምሳሌ ነው።ጌታችን በቸርነቱ በቀኙ ከሚቆሙት ጋር ያቆመን ዘንድ መልካም ፈቃዱ ይሁንልን።

## *ፃኡ ንኡሰ ክርስቲያን*

ንኡሰ ክርስቲያን የሚላቸው የሃይማኖት እና የምግባር ተብለው ይከፈላሉ።የሃይማኖት የተባሉት ሳይጠመቁ እድሜያቸው ትልቅ የሆኑ ሰዎች ወደ ትክክለኛዋ ወደ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ሲመጡ አዕማደ ቤተክርስቲያንን እየተማሩ እስከ 3 ዓመት ይቆያሉ። በዚህ በሦስት ዓመት ውስጥ ቅዳሴ እስከ ፍሬ ቅዳሴ ድረስ ይቆዩና ፍሬ ቅዳሴ ሲጀመር ንኡሰ ክርስቲያን የሆናችሁ ውጡ ይባሉና ይወጣሉ። ይኸውም በዚሁ በሦስቱ ዓመት ውስጥ ነው እንጂ ከተጠመቁ በኋላ አይደለም።ከፍሬ ቅዳሴ በፊትስ ለምን ይቆያሉ ቢሉ ከዚያ በፊት ያለው የቅዳሴ ክፍል በስፋት ትምህርት ያለበት ነው።እንዲማሩ ነው።ከፍሬ ቅዳሴ በኋላ ግን የተጠመቁት ብቻ የሚቀበሉት ቁርባን የሚፈተትበት ስለሆነ ሙሉ በሙሉ አምነው ተጠምቀው እስኪመጡ ድረስ አይቆዩም።

ሁለተኛው ንኡሰ ክርስቲያን የሚባሉ የምግባር ናቸው።የተጠመቁት ምእመናን ኃጢአታቸውን ለመምህረ ንሥሓቸው ነግረው ንሥሓ አባታቸው በቀኖና እስከዚህ ቀን ድረስ በበረሀ ሁናችሁ እስከዚህ ቀን ድረስ በአጸደ

ቤተክርስቲያን ሆናችሁ እያስቀደሳችሁ ስትጨርሱ ከቤተክርስቲያን ገብታችሁ ሥጋውን ደሙን ተቀበሉ የሚባሉት ናቸው። በበደሉት በደል ምክንያት ለተወሰኑ እለታት በቀኖና ቤተክርስቲያን እንዳይገቡ የሚከለከሉ ንኡሰ ክርስቲያን ይባላሉ።

መጋረጃ ወይም መንጦላእት የረድኤተ እግዚአብሔር ምሳሌ ነው። የቤተክርስቲያን ሦስቱ በሮች የሦስቱ ሥላሴ ምሳሌ ናቸው። ደጀ ሰላም የምትባለው በምዕራብ አቅጣጫ ከመግቢያ በር ላይ የምትገኝ ቤት ናት።ምሳሌነቷ የገነት ነው። ቀሳውስት ደጀሰላም ትንሽ ቆይተው ወደ ቤተክርስቲያን እንዲገቡ ቅዱሳንም እስከ እለተ ምጽአት ድረስ በገነት ቆይተው በኋላ በክብር ወደምትበልጠው መንግሥተ ሰማያት የመግባታቸው ምሳሌ ነው።ሌላው በቤተክርስቲያን ጉልላት ላይ የሚደረገው የሰጎን እንቁላል የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነው።ምሳሌነቱም እንዲህ ነው።ሰጎን እንቁላል ከጣለች በኋላ እስኪፈለፈሉ ድረስ አትለያቸውም። ምግቧን ለመፈለግ ስትሄድ እንኳ ባሏን ተክታ ነው። ለአንድ አፍታ ከእይታ ውጭ ካደረገቻቸው ግን እንቁላሉ ይበላሻል።ሰጎን የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነው። እንቁላሎቹ የምእመናን ምሳሌ ናቸው። መንፈስ ቅዱስ እኛን ሁልጊዜም እንደሚጠብቀን ያስረዳናል።

# ክብረ ቅደሴ

ሀሌ ሉያ ማለት ቅድመ ዓለም የነበረ ዓለምን አሳልፎ የሚኖር ማለት ሀሌ ሉያ ማለት ስብሐት ለእግዚአብሔር ለእግዚአብሔር ምስጋና ይገባል ማለት ነው።በቅዳሴ በማኅሌት ብዙ ጊዜ የምንሰማው ቃል ስለሆነ ብናውቀው መልካም ነው ብየ አስባለሁ።አንድ ባሕታዊ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ከምስጋናሽ ሁሉ ማንን ትወጃለሽ ብሎ ጠየቃት።እርሷም ልጄ መድኃኔዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ መዝሙረ ዳዊትንና አቡነ ዘበሰማያትን

የሚደግምን  ሰው በጣም እንደሚወደው ሁሉ እኔም ውዳሴ ማርያምን እና ቅዳሴ ማርያምን የሚጸልይ ሰውን እወደዋለሁ ከልጄ ከወዳጄ ከኢየሱስ ክርስቶስ አማልጄም ጸጋ በረከት ረድኤት አሰጠዋለሁ ብለዋለች።

ቅዳሴ የሚቀድስ ሰው እግዚአብሔርን የሚቀድስ አይምሰለው ራሱ ይቀደሳል እንጂ እንዲል።እግዚአብሔርን ብናመሰግን ለእግዚአብሔር የሚጨመርለት ምንም ነገር የለም። እኛ ግን በማመስገናችን የምናገኘው ታላቅ ጥቅም አለን። ምስጋናን ወይም ቅዳሴን ሊቃውንቱ የመላእክት ምግብ ይሉታል።ወኀብስተ መላእክቲሁ በልኡ እጓለ እመሕያው የሚለውንም።የመላእክትን እንጀራ ምስጋና ሰዎች ስቡሕ ውዱስ እያሉ አመሰገኑ ማለት ነው። ሁልጊዜም ቢሆን ንሥሓ እየገባን እያስቀደስን ልንቆርብ ይገባናል።በቅዳሴ ጊዜ ማውራት ውርውር ማለት እና እንደጠቅላላው ቤተክርስቲያን ውስጥ አለማዊ ነገር ልንነጋገር አይገባንም።በቅዳሴ መካከል ይጫወቱ የነበሩ ሕጻናትን እንኳ መልአክ እንደቀሰፋቸው መንፈሳውያት መዛግብት ያስረዳሉ። ስለዚህ ሕጻናትንም ሥርዓት እንዲማሩ እንዲያውቁ ልናስተምራቸው ይገባል።

በነገራችን ላይ ከዚህ የተወሰነውን ነገር ነው የጻፍኩት ዝርዝር ጉዳዮችን እና ዋና ዋና ጉዳዮችን ለማየት የ14ቱ ቅዳሴያት መጽሐፍ አንድምታ የሚለውን መጽሐፍ ገዝታችሁ ማንበብ ትችላላችሁ።ከዚህ እንዳው ለማስተዋወቅ ያህል ነው እስከ ክፍል 6 የጻፍኩት እንጂ ብዙ ጥሩ ጥሩ ነገሮቹን ለማግኘት ሙሉውን መጽሐፍ እንድታነቡት እጋብዛለሁ።

# ትንሣኤ ልብ

የኢትዮጵያን ትንሣኤ ለማየት ከፈለግን መጀመሪያ የእኛ የእያንዳንዳችን ልብ ትንሣኤ ያስፈልገዋል።

**1ኛ ጸሎት**፡-ጸሎት ከፈጣሪ ጋር መነጋገር ነው። ስለዚህ ከፈጣሪ ጋር ከመነጋገር የበለጠ ምንም ነገር ስለሌለ ከማንኛውም ነገር በፊት ቢያንስ በ7ቱ ጊዜያት (3, 6, 9, 12, 3, 6, 12) ሰዓት መጸለይ አለብን።ጸሎት ምስጋና ያለበት ልመና ነው።ፈጣሪ በቸርነቱ ስላደረገልን ነገር ሁሉ በፍቅር ማመስገን አለብን። መላእክት ይህን ሁሉ ጸጋ የሰጣቸውን ፈጣሪ በፍቅር ያመሰግኑታል። ተፈጥሮን እንድንኖርባት የሰጠን አካላችንን ካለመኖር አምጥቶ የሰጠን ለእኛ የሚያስፈልጉን አየርን ውሃን እና ሌሎች ነገሮችን የሰጠንን ፈጣሪ ማመስገን ይገባል።

**2ኛ ይቅርታ**፡-ከፈጣሪ ውጭ ያሉ ፍጥረታት በሙሉ ፍጹም አይደሉም ሊሳሳቱ ይችላሉ።በዚህን ጊዜ እኛም ብዙ ስህተቶችን እንደሰራን በማስታወስ ፈጣሪ ግን በቸርነቱ በይቅርታ ይቅር እንዳለን በማሰብ እኛም በሌሎች ላይ ስህተት የመሰለ ነገር ስናይ ከቂም ከበቀል ይልቅ በይቅርታ ልብ አይተን ፈጣሪ እኛን ይቅር እንዳለን እነርሱንም ይቅር እንዲላቸው በርኅራኄ ማየት ነው።

**3ኛ ፍቅር፡-** ይህ እግዚአብሔርን መውደድ እና ሰውን መውደድ ተብሎ ይከፈላል። እግዚአብሔርን መውደድ ማለት ለትእዛዞቹ መገዛት ሲሆን ሰውን መውደድ ማለት ደግሞ በእኛ ሊደረግብን የማንፈልገውን በሌሎች እንዲደረግ አለመፈለግ እና አለማድረግ ሲሆን በአንጻሩ ለእኛ ሊደረግልን የምንፈልገውን የምንመኘውን ነገር ለሌሎችም መመኘትና ማሰብ ነው።

**4ኛ እውነት፡-** እውነት ማለት ውሸትና ግምት ያልተቀላቀለበት ግነት የሌለበት ነገሩን እንደነገርነቱ ብቻ በጥራት ማቅረብ መናገር ማለት ነው።ከሰዎች ክብርን እና አድናቆትን ሽተን ወይም ሰዎችን ለማበሳጨት ወይም ለማስደሰት ብለን ያልተደረገን ነገር በልብ ወለድ ወይም በእውነቷ ላይ ጨመርመር እያደረጉ ማውራት ውሸት ስለሆነ ልንተወው ይገባል።

**5ኛ ጾም፡-** ጌታችን ዝንቱ ዘመድ ኢይወጽእ ዘእንበለ በጾም ወበጸሎት ብሎ እንደተናገረው ክፉ ሀሳቦቻችንን ከአዕምሮ ለማስወጣት ጾም ወሳኝነት አለው።ጾም ማለት በተወሰነ ጊዜ ከምግብ በተወሰኑ ዕለታት ከጥሉላት መከለከል ለዘላለም ደግሞ ክፉ ከማየት ክፉ ከመስማት አጠቃላይ ሕዋሳቶቻችንን ከክፉ ነገር መጠበቅ ነው።አእምሯችንን ከሚበክሉ ነገሮች መራቅ ነው።

**6ኛ ቁርባን፡-** የሰው ልጅ የሚቀደሰው ንሥሓ ገብቶ የጌታችንን ክቡር ሥጋውን ክቡር ደሙን በልቶ ጠጥቶ ነው።በዚህም አምላክ የጸጋ ውኅደት ይዋሐደናል። መልካሙን መንገድም ይመራናል።

**7ኛ ተግባረ ዕድ፡-** ይህም ማለት በዚህች ምድር እስካለን ድረስ የምንበላውን የምንለብሰውን እና ሌሎች ለሥጋችን አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ለማግኘት መስራት ነው።ጌታም ጥረህ ግረህ ብላ ብሎናል።ስለዚህ ከፈጣሪ ሕግ የማያወጡ ሥራዎችን ማረስ መቆፈር ማስተማር መጻፍ ማከም ሕንጻ መስራት ወዘተ የመሳሰሉ ስራዎችን መስራት ነው።

**8ኛ ንሥሓ፡-** ይህ ደግሞ ቅጣት እንደሚያስቀጣ እያወቅን በድፍረት ሳናውቅ በስህተት የሰራነውን በደል በንሥሓ አባቶቻችን በኩል ተናግረን ቀኖና ተቀብለን እግዚአብሔርን ይቅርታ ጠይቀን ወደ መልካም ስራዎች

የምንገባበት በር ነው።ንሥሐ መጸጸት ማለት ነው።ምን ነክቶኝ ነው ይህን ክፉ ስራ የሰራሁት ብለን ጌታዬ ሆይ በቸርነትህ ማረኝ የምንልበትና ጥፋታችንን ለማረም እና መልካም ስራ ለመስራት ከፈጣሪ የሚሰጥ ሁለተኛ ዕድል ነው።ወድቄ ልሰበርና እጠገናለሁ እንደማንል ሁሉ።ኃጢአት ልስራና ንሥሐ ልግባ ግን አይባልም። ኃጢአት ለመስራት አቅዶ ንሥሐ ለመግባት ማሰብ አይገባም።እስከዛሬም አድርገነው ከሆነ ለዚህም ንሥሐ ገብተን ሕይወታችንን ማስተካከል ይገባናል።

**9ኛ ትሕትና፡-** ይህ ደግሞ እኛ በብዙ መንገድ ደካሞች አላዋቂዎች መሆናችንን አውቀን በሌሎች አለመፍረድን ያካትታል።አለማወቅ ስለሚገድበን ፈጣሪ በተለያዩ አምሳላት ስለሚገለጽ ለማንኛውም ሰው ራስን ከልብ ዝቅ ማድረግ ነው።ሁሉም ሰው ከአንተ የከበረ እንደሆነ አስበህ መኖር ማለት ነው።ትሕትና ደካማነታችንን አውቀን ረድኤተ እግዚአብሔርን መሻት ነው።

**10ኛ ትዕግሥት፡-** ይህ ደግሞ ነገር አላፊ ቻይ መሆን ማለት ነው።ክፋትን በክፋት ላለመመለስ መታገል ነው። ሰው ሲሰድበን መልሰን ላለመስደብ ፈጠን ፈጠን የሚል ሕዋሳታችንን መግታት ነው። ወዘአዝለፈ ትዕግሥቶ ውእቱ ይድኅን ብሎናል ጌታችንም።

በነገራችን ላይ ልባችን ከተመለሰ እንደ ፈያታይ ዘየማን በአጭር ጊዜ ገነት የሚያስገባንን ስራ መሰራት እንችልለን።ቂርቆስ ታላቅ ሰማእት ለመሆን በዚች ምድር የኖራት 3 ዓመት በቂ ነበረች።እኛም ቀሪ ዘመናችንን 1 ቀንም ትሁን 1 ሰዓት መልካም ሰርተንባት እንለፍ።

ረድኤተ እግዚአብሔር አይለየን።
የቴሌግራም ቻናሌ በትረ ማርያም አበባው
https://t.me/betremariyamabebaw ነው።

አነሳስቶ ላስጀመረን
አስጀምሮም ላስፈጸመን
ልዑል እግዚአብሔር
ምስጋና ይገባል።